# **ለመልአከ መንክራት ቀሲስ ግርማ ወንድሙ እንኳን ደስ አለዎት፤**

አባቶቻችን ነቢያት፣ሐዋርያትና ቅዱሳን ሰማዕታት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በሰጣቸው ሀብተ መንፈስ ቅዱስ እያታገዙ በአደባባይ በአልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ የተያዙትን በሽተኞች በመፈወስ፣ ልቦናቸው የናወዘውን በማጽናናት፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን በማነጽ፣ የአምላክን ፍቅር፣ሰላማዊ ቃል ዜና ማዋዕሉን በማብሠር፤ ገቢረ ታአምራቱን በማወጅ ለሚሰጡት መንፈሳዊ አገልግሎት የሚከፈላቸው ትልቁ ደመወዝ የሀሰት ክስ፣ እስራትና እንግልት ነበር።

ሳውል ሲፈጽመው ከንበረው ወንጀል፣ ወድቆ ከነበረበት የሐጥያት ቀንበር አምላካችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱ **ሳውል! ሳውል! ሳውል! ስለምን ታሳድደኛለህ** ብሎ ጠርቶ **ጳውሎስ** የሚል ስያሜ ሰጥቶ መለኮታዊ ሐልዎቱን አብርቶ፤ ተዘዋውሮ እንዲያስተምር ኃይል ሰጥቶ፣ ኅሙማንን እንዲፈውስ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ተቀናጅቶ፤ **ጳውሎስ** ብዙዎችን አሳመነ ከደዌያቸውም ፈውሳቸው፣ ብርሃናዊ ቃሉን ሰበከ አስተማረ ኃይለ አጋንንትን በመዶሻ ሰባበረ ነገር ግን የዚህ ሁሉ መንፈሳዊ ተግባር ውጤቱና ደመዎዙ እስራት ነበር፤ በመጨረሻም ስለፈጣሪ  ሕይወቱን አሳልፎ በሮም አደባባይ በሰይፍ ተቀልቶ ሞተ።

በመሆኑም በዘመናችን እግዚአብሔር በሰጠዎት ሀብተ ክህነት በአልጋ ቆራኛ በደዌ ዳኛ የተያዙ ብሽተኞችን፣ ቀኑ ጨልሞባቸው በእርኩስ መንፈስ በአደገኛ ሱስ ተይዘው ሕይወታቸውን መምራት ያልቻሉትን፣ እያላቸው የሚበሉት ያጡትን፣ አፍ እያላቸው መናገር የተሳናቸውን፣ ጉልበት እያላቸው ሽባ ሆነው የሀገርና የወገን ሸክም የሆኑትን ወገኖችን ሁሉ በሀገር ውስጥና በሀገር ውጪ በተጨባጭ ማስረጃ ግልጽ በሆነ አደባባይ **ከመስቀል በስተቀር ምንም ሳይጨብጡ** እግዚአብሔር በፈቀደ መጠን በሚሰጡት መንፈሳዊ አገልግሎት ምክንያትና ወንጀል ሆኖበዎት ለቀደሙት ሐዋርያትና ቅዱሳን ሰማዕታት የተከፈልለውን ትልቁን ደመዎዝ ተከፋይና ተሳታፊ በመሆነዎት **እንኳን ደስ አለዎት እላለሁ።**

በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንጋፋ ሊቀ ጳጳስ የሆኑትና መንፋሳዊ አባትነታቸው ፀሐይ ከሚመስለው መልካቸውና ተክለ ሰዎነታቸው ጋር የተዛመደው ገዳማዊው የማኅበረ ስላሴው ገዳም አበእምኔትና በጎንደር ክፍለ ሀገር ቋራ አካባቢ ተወልደው ያደጉት ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አባ ዮሴፍ፤ ከሳምንታዊ የግል ጋዜጠኛ በወቅቱ በነበረው የቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ብዙ ጥያቄዎችን ቀረቦላቸው ነበር። ብፁዕ አባ ዮሴፍ  ማንንም ሳይፈሩ ጥያቄዎችን ሁሉ በተገቢው ምላሽ እወነቱን ተናገሩ። ጋዜጠኛው ስለሊቀ ጳጳሱ ሕይወት አዝኖ፤ **«አባታችን የበላይና የበታች ሳይፈሩ ይህን ሁሉ እውነት የሚናገሩት ለራስዎትና ለሥራዎት አይሰጉም»** አላቸው። አረጋዊው ሊቀ ጳጳሳ አባ ዮሴፍ **«እውነትን መስክሮ መሞት ከቅዱሳን አባቶቸ ከሐዋርያት የተማርኩት ነው።»** በማለት መልስ ሰጥተዋል። ይኸው ቃላቸው በተቀበሩበት መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ከሀውልታቸው ላይ ተጽፎ የዘመናችን መሪና አስተማሪ ኃይለ ቃል ሆኖ ይገኛል። ቤተ ክርስቲያንን የተሳለመ ሁሉ ይን ቃል ያነባዋል እውነትን የመናገር መንፈሳዊነትን በቀላሉ ይማራል። በመሆኑም እርሰዎ መልአከ መንክራት ቀሲስ ግርማ የተከሰሱበት እውነትንና ታላቋን ቤተ ክርስቲያን የሀብተ ክህነት ተስፋ መንፈሳዊ አገልግሎት በተግባር በመተርጎመዎ የተከፈለዎት የሐዋርያት ትሩፋት ደመዎዝ በመሆኑ **እንኳን ደስ አለዎት።**

ዛሬ **የእምነት ጎህ ቀዳጅ ዋልታ፣ ሀገር አድነት ባለውለታ፣የታሪክ መዛግብት አለኝታ፣ የዕውቀት ገብታ** የሆነችው ታላቋ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች **ከሰባት ሚሊዮን** በላይ መቀነሳቸው የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ሊቃነ ጳጳሳት በሚገባ ጽፈውታል፤ የታሪክ ተወቃሽ እንዳንሆን በማለት አስጠንቅቀዋል። አሁን በቅርቡ በሰላሳ አራተኛው  አጠቃላይ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔ ስብሰባ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ **የምዕመናኑ ቁጥር መቀነስና መባዘን ያሳሰባቸው መሆኑ በአጽንዖት ገልጸዋል።**

በዚህ ፈታኝ ጊዜ **በዕውቀታቸው ከሚመጻደቁት መካከል ሳይሆ ከደካሞች መካከል  እግዚብሔር እርሰዎን አስነስቶ** በሀብተ ክህነት ላይ የሰጠውን ኃይል አበርቶ የቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ከተያዙበት ደዌ፣ ከያዛቸው ከእምነታቸ ካሰደዳቸው አጋንንት እያጠመቁ እያዳኑ ከጠፉበት በረት ተመልሰው እዲገቡ በማድረገዎት፤ በልዮ ልዮ መንገድ የጠፋውን ምዕመናን መልሶ በመፈለግ በሚችሉት መጠን በመንፈሳዊ የሀብተ ክህነት አገልግሎት ቤተ ክርስቲያኗ ቀዳሚ ሐዋሪያዊት መሆንዋን ለውጪ ሀገር ሰዎች ችጭምር በታሪክ ብቻ ሳይሆን በተግባር ለማስተዋወቅ መታደለዎት፣ የሰው ልጆች ከወደቁበት አዘቅት ወጥተው ጤናማ ሕይወታቸውን እንዲመሩ በማድረገዎት ለዚህም የቀደሙት ሐዋርያት የተሰጣቸው የእስራት ክፍያ በማግኘተዎት **እንኳን ድስ አለዎት።**

በአሁኑ ወቅት አንዳንድ በማስመሰል ክህነት እየተቀበሉ የክህነት አርማ እየደረቡ በቤተ ክርስቲያንና በእግዚአብሔር መካከል የተሰጣቸውን ከባድ መንፈሳዊ አደራ ዘንግተው የገቡትን ቃል ኪዳን ሽረው ከህነቱን የግል ጥቅማቸው ማስፈጸሚያ ከማደረግ በስተቀር ለቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ ሆነው ባልተገኙበት፤ ይልቁንም እነሱ በሚፈጽሙት ተግባረ እየተሰናከለ ከዋሐርያዊት ቅድስት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በረት እየወጣ ጫካ የሚገባና በአውሬዎች የተነጠቀው ቁጥር እየበዛ በመጣበት፣ የተከፋፈለውና የተለያየው የመንጋው አካል መጠነ ሰፊ በሆነበት፤ በተለይም ገለልተኛ ቤተ ክርስቲያን እያሉ እያዋቀሩ በቤተ ክርስቲያን ጉልላት የተደራጁ ግለሰቦች ደገኛውን አማኙን ሕብረተሰብ የሚያታልሉት ብዙዎች በሆኑበት፤ **ከእነ ጭራሹም እኔ በምኖረበት በለንደን ከታማ በቅዱስ ሲኖዶስ ቡራኬ የተመሠረተችውን ቅድስት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ሽጠው ለመከፋፈል ለፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀረቡ «ካህናት»  መሰል ተቃዋሚ ፓለቲከኞችና ተከታዮቻቸው በአመጽ በሰከሩበት በአሁኑ**

**ዓይን ያወጣ የክህደትና የፈተና ዘመን፤** ምዕመናን ተዘዋውረው በማስተማረዎ በእግዚአብሔር ፈቃድ የታላቋን ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ፀጋ በረከት ተካፍለው ማካፈለዎ፣ ምዕመናን በሚችሉት መንገድ በአግባቡ በመጠበቀዎ የጠፉትን በመፈለገዎ የተከፍለዎ የእስራት ደመዎዝ በመሆኑ **እንኳን ደስ አለዎት።** ቅዱስ ሲኖዶስ በዓመታዊ የጥቅምት ጉባዔ ላይ እንዳለ አውቃለሁ፤ እርሰዎን መልአከ መንክራት ቀሲስ ግርማ ወንድሙን ክህነት ሰጥቶ ለአገልግሎት እዳሰማራዎት እንረዳለን፤ አገልግሎተዎንም የሚፈጽሙት በቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ መሆኑ ይታወቃል። የሚሰጡት አግልግሎትም በቅዱሳት መጽሐፍት የተነገረ በቀኖና ሐዋርያት የተደገፈ የማጥመቅና የመፈውስ መንፈሳዊ አገልግሎት መሆኑን ይታመናል። ለዚህም ብዙዎች ጠንካራ የሚባሉ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ምስክርነታቸውን ሲሰጡ ቆይተዋል።

**ቅዱስ ሲኖዶስ ለዕርሰዎ ለቀሲስ ግርማ ምን ዓይነት የአገልግሎት መመሪያና የሥራ ዝርዝር እንደሰጠዎት አላውቅም። አግልግሎተዎት ሰፊ ተገልጋዮቹም በርካታ እንደመሆኑ መጠን አገልግሎተዎትን የሚያጠናክር ልዮ መመሪያ እንደሚስፈልገዎት እረዳለሁ።** ሆኖም **ሰብሕዎ በክህሎቱ ነውና** በሚችሉትና እግዚአብሔር በፈቀደለዎት መጠን በዚህ የማጥመቅ አገልግሎት ተሰማርተው የቤተ ክርስቲያንኗ አንጡራ ሀብት የሆኑት ምዕመናንን እያገለግሉ ቆይተዋል። አሁንም እያገለግሉ እደሚገኙ ለማንም ግልጽ ነው። በዚህ መንፈሳዊ አገልግሎተዎት በሀገር ወስጥ ብቻ ሳይሆን በውጪ ሀገር ጭምር ታውቀዋል። በዘመናችን በሳይንሳዊ ጥናት የላቀ ዕውቀት አለን የሚሉት ሁሉ እስኪደንቃቸው ድረስ ብዙ በሽተኞችን በእንግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈወሱ ምክንያት ሆነዋል።

ቅዱስ ሲኖዶስ እርሰዎ የሰጡት መንፈሳዊ አገልግሎት ሁሉ በተሰጠዎት ክህነት በመሆኑ እያንዳንዷ አግልግሎት ቤተ ክርስቲያንኗን ወክሎ የተከናወነ በመሆኑ ከሁሉም በላይ የቤተ ክርስቲያንኗን ሐዋርያዊነት ይበልጥ በተግባር ያስተዋወቁ መሆነዎትን እንደሚረዳ ተስፋ አደርጋለሁ። ከዚህ አንጻር የቀረበበዎት ክስ እንደተመለከትነው ሆን ተብሎ የተቀነባበረ እንደሆነ በመረዳት ወይም በትክክል መጣራት እንዳለበት ሰፊ ትኩርት ይሰጥበታል ብዬ አስባለሁ። ምንም እንኳን እርሰዎ ቀሲስ ግርማ ከቀደሙት ሐዋርያት የበለጠ ሕይወት ባይኖረዎትም፤ የአባቶቻችን የሐዋርያት ጉባዔ የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ በዚህ ወቅት አብሮ የመታሰር ስሜት ወይም እንደ እኔው **እንኳን ድስ አለዎት** በማለት በደሉን ማሰማት ብሶቱን በማጽናናት በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚፈቱበትን መንገድ ማመቻቸት ይኖርበታል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። እሁንም በድጋሜ ለተከፈለዎት የገልግሎት ዋጋ **እንኳን ደስ አለዎት።**

መንግሥት ወንጌልን የሚሰብኩ፣ በአልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ ተይዘው ለሀገርና ለወገን ሸክም የሆኑትን ወገኖች በተሰጠዎት ፀጋ በመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ምክንያተ የድህነት ክህነታዊ የምክር አገልግሎት የሚሰጡ መሆነዎትን፤ በኢጋንንትና በአድንዛዥ ዕጾች ተወጥረው አስቸጋሪ ዜጋ የሆኑትን መልሶ በማነጽ የሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ ተሳታፊ ኃይል እንዲሆኑ የሚያደርጉትን መንፈሳዊ ጥንካሬ በማስተዋል፣ ዜጎችን በጤነኛ አስተሳሰብ መልሶ የማቋቋምና በሞራል ግንባታ የሚያደርጉትን አስተዋጽዖ በማጤን፣ ሁሉም በወንጌል ተመርቶ በሰላምና በፍቅር በመረዳዳትና በመፈቃቀር አንዱ አንዱን እንዳይበድል በመምከር ከፓለቲካ የፀዳ ትምህርት በማስተማረዎት፣ በጠቅላላው ሰዎች የተረጋጋ ሰላማዊ ግኙኙነትና በጸሎት ላይ የተመሠረተ ሕይወት እንዲኖራቸው ምክር በማደረግ፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም **ጎሳ፣ ዘር፣ ቀለም፣ የትውልድ ቦታና ሀገር ሳይለዩ** የሚሰጡትን አገልግሎት በሕግና በሥርዓት የተከበረና ተጠናክሮ የሚቀጠልበትን ሁኔታ ማበረታት እንደሚገባው ይሰማኛል።

ይሁን እንጅ የሀሰት ከሳሾች ተነስተው ብዙዎችን የሚያገለግሉትን መንፈሳዊ አባት ምክንያት ፈልጎ ዘብጥያ መጣል የማይገባ ተግባር መሆኑን ሁላችንም ተረድተነዋል። ይህ አስከፊ ተግባር ከቅዱሳን ሐዋርያት አባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ትሩፋት በመሆኑ **እንኳን ደስ አለዎት።** ሆኖም በሥጋዊ አስተዳደር ያሉት መሪዎች አሁንም በድጋሜ በሰፊ አዕምሮ በሰከነ ልቦና አጥንተው በአጭር ጊዜ ውስጥ በሰላም ተለቀው የሚሰጡትን መንፈሳዊ አገልግሎት ከማዳከም ይልቅ በመደገፍ እንዲያጠናክሩት ከልብ እመኝለዎታለሁ።

እኔ በግሌ በበኩሌ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይነቴና ወዳጅነቴ እግዚአብሔር በፈቀደ መጠን የሰጡትን መፈሳዊ አገልግሎት በማስታዎስ በበሽታ የጠወለገውን፣ በጋንንት የተከበበውን፣ በምጥፎ ሱስ የዛለውና የተበላሸውን ዜጎቻችንና የውጪ ሀገር ሰዎችን ጭምር መንፈሳዊ ሕይወት መልሶ በማነጽ ቀኖና ሐዋርያት በሚፈቅደው መሠረት በሀብተ ክህነት በመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ሲያገለግሉ በመቆየተዎ ምክንያት በዘመናችን የቅዱሳን ሐዋርያት በረከት የሆነው የሀሰት ክስ እስራት ደመዎዝ ስለተከፈለዎ **መልአከ መንክራት ቀሲስ ግርማ ወንድሙ እንኳን ደስ አለዎት** በማለት መንፈሳዊ መልዕክቴን አስተላልፋለሁ። **እግዚአብሔር እርሰዎን መሣሪያ አድርጎ ከበሽታቸው የፈወሳቸው ሰዎች አምላክ እንዲረዳዎት ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን!**

**መጋቤ ጥበብ መንገሻ መልኬ**

**እወነት በቃሉ**

**ላዕለ ፈጣሪሁ ተበታአምኖ ይሄሉ።**

**ጥቅምት 19 ቀን 2008 ዓ.ም፤ ዘመነ ዮሐንስ ወንጌላዊ፤ ሎንደን፤**